የሰ/መ/ቁ. 28254

ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ፀጋዬ አስማማው

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አትናቦን ነጋሳ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** መኮንን መስፍን ከጠበቃ በሻዳ ገመቹ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ውልን መነሻ ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ተከሣሽ የመድን ዋስትና የገባለት የሠ.ቁ. 3-28204 አ.አ. የሆነ መኪናዬ በመገልበጥ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ተከሣሽም በገባው ግዴታ መሠረት ከወደቀበት ቦታ አስነትቶ በማምጣት በሪከቨሪ ክፈሉ ያስገባው ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ሊያስጠግንልኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በገባው የውል ግዴታ መሠረት መኪናውን አስጠግኖ እንዲያስረክበኝ ወይም የመኪናውን ሙሉ ዋጋ እንዲከፍለኝ መኪናው የንግድ መኪና በመሆኑ እና ተከሣሽም በተገቢው ጊዜ ለመጠገን ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ የተቋረጠ ጥቅም ታስቦ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የመድን ዋስትና ውል መግባቴ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን መኪናው የተገለበጠው በውሉ የተደረገውን ስምምነት በመጣስ ተሳቢ ሲጎትት በነበረበት ጊዜ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም፡፡ የመድን ዋስትና ውሉ የተቋረጠ ገቢ እንዳይጠየቅ የሚከለክል በመሆኑ የተቋረጠ ጥቅምን በሚመለከት የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተቋረጠ ጥቅም ስም የተጠየቀው የገንዘብ መጠንም የተጋነነ ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተከሳሽ በገባው ውል መሠረት የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ መኪናውን አስጠግኖ ወደነበረበት በመመለስ ለከሣሽ ያስረክብ፣ በገባው የውል ግዴታ መሠረት መኪናውን ለማስጠገን ፈቃደኛ ባለመሆኑ የተቋረጠውን ጥቅም ብር 56,300 ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ ከዚህ በኋላ መጀመሪያ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪም በበኩሉ በተቋረጠ ጥቅም ስም የተወሰነው ገንዘብ አንሶአል በሚል መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቦአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሁለቱም በኩል የቀረቡትን ይግባኞች መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም መኪናውን አስጠግኖ ለተጠሪ ያስረክብ፡፡ እንደዚሁም ተቋረጠውን ገቢ ብር 275,000 ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ኀዳር 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ በመደረጉም ሆነ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፍል የተሰጠውን ውሣኔ የሕግ አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የመድን ዋስትና ውል ስለመኖሩ አላከራከረም፡፡ ዋስትና የተገባለት መኪና በስራ ላይ እንዳለ መገልበጡንና በዚህ የመገልበጥ አደጋ የተነሣም ጉዳት የደረሰበት መሆኑም አከራካሪ

አይደለም፡፡ አመልካች ውሉን መሠረት በማድረግ መኪናውን ከወደቀበት ቦታ አስጎትቶ በማምጣት ወደ ረከቨሪ ክፍሉ ካስገባው በኂላ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው ወደ ክርክር የገባው፡፡ ክርክሩን በየደረጃቸው የሰሙት የስር ፍ/ቤቶችም አመልካች ኃላፊነት የለብኝም ለማለት በመከራከሪያነት ያነሳውን ነጥብ እግምት ውስጥ በማግባት ክርክሩን ከመምራታቸውም በላይ፣ በግራ ቀኝ ወገኖች በኩል የተቆጠሩትን ማስረጃዎችንም ሰምተዋል፡፡ በመጨረሻም ማስረጃዎቹን በማመዛዘን በተሻለ ሁኔታ ያስረዳው ተጠሪ እንደሆነ በመገንዘባቸው የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርገዋል፡፡ አመልካች የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት እንዳለበትም አረጋግጠዋል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ኃለፊነት የለብኝም ለማለት በመከራከሪያነት ያነሳው ነጥብ በግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ማስረጃ አንፃር ታይቶ እና ማስረጃውም ተመዝኖ እልባት አግኝቶአል፡፡ የሰበር ችሎት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች አግባባነት ሊመረምር የሚችለው በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት አለ ሲባል ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን አመልካች ያቀረበው አቤቱታ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ ስህተት ተፈጽሞአል ከሚል ያለፈ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል በሰጠነው ምክንያት የምንመረምረው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለትም አልቻልንም፡፡

ከዚህ በመቀጠል የመረመርነው ተጠሪ በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ በላይ እንዲከፈለው ተወስኖለታል በማለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ነው፡፡ ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው የክስ ማመልከቻ የተቋረጠ ጥቅም በማለት እንዲከፈለው የጠየቀው ገንዘብ ብር 130,400 /አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንደነበር ከመዝገቡ አረጋግጠናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን መነሻ በማድረግ እና የመኪናው



የዓመት ገቢ ነው ያለውን መጠን እግምት ውስጥ በማግባት አስልቶ የተጠየቀው ብር 130,400 ያነሰ ገንዘብ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ተጠሪም በክሱ የጠየቀውን የገንዘብ መጠን ሳይለውጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው ገንዘብ አንሶኛል በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦአል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ገንዘቡ ያንሳል ወይስ አያንስም የሚል ጭብጥ በመያዝ በእርግጥ ተጠሪ ከመኪናው በዓመት የሚያገኘው ገቢ ወይም ጥቅም ምን ያሕል እንደሆነ ለማጣራት በራሱ በኩል ማጣራቱና ማስረጃም መስማቱ ትክክል ነው፡፡ በዚህ ረገድ ፍ/ቤቱ ስህተት ፈጥሮአል ማለት የሚቻለው ተጠሪ ከጠየቀው በላይ ገንዘቡን ወደ ብር 275,000 ከፍ አድርጎ በመወሰኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህኛውን የውሣኔው ክፍል ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመጨረሻም የመድን ዋስትና ውሉ የተቋረጠ ጥቅም እንዳይጠይቅ ይከለክላል የሚለውን የአመልካች ክርክር ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ በውሉ ላይ ይህን መሰል ስምምነት ስለመደረጉ የተካደ አይደለም፡፡ ነገር ግን አመልካች መኪናውን አስጎትቶ ካመጣና አስጠግናለሁ በሚል እሳቤ ሪከቨሪ ክፍሉ አስገብቶ ከቆየ በኂላ ለማስጠገን ፈቃደኛ አይደለሁም በማለቱ ተጠሪ ወደ ክስ እንዲያመራ አስገድዶታል፡፡ መኪናው በንግድ ስራ ላይ ተሰማርቶ የነበረ በመሆኑ በመቆሙ ምክንያት በተጠሪ ላይ ከፍተኛ ኪሣራ እንደሚደርስ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አንድ ተዋዋይ ወገን እንደ ውሉ ሳይፈጽም ቢቀርና በዚህ ምክንያትም በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ላይ ጉዳት ቢደርስ የመካስ ኃላፊነት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1771/2/ የተቀመጠው ድንጋጌ በግልጽ ያመለክታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች እንደ ውሉ ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ በተጠሪ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ሆኖአል፡፡ ከዚህ የተነሣም እንደ ውሉ ይፈጽማል የሚል ግምት ተይዞ የተቀመጠውን የውሉን አንድ አንቀጽ በመጠቀም ኪሣራውን ከመክፈል ነፃ ሊሆን የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት